

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንቢያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከጁን 1-10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ እንዲሁም

## ከጁን 11-20/2025 እና ከጁን 21-30/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

## ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁን 2025

አዲስ አበባ


## 1. እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉ እና በምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በሀዋሳ 22፣ ጎሬ 31.4፣ 25፣ ጅማ 39.4፣ ነቀምት 31.4፣ 44.6፣ 69፣ አይራ 23.4፣ አማን 23.4፣ 25.4፣ 21.9፣ አንገር ጉቲን 38፣ 54.2፣ 32፣ 26.4፣ አርጆ 26.2፣ 28.4፣ 26.4፣ አየሁ 52.6፣ ቦሬ 47.2፣ ቡርጂ 21.1፣ ቻግኒ 22.2፣ ጨዋቃ 25.6፣ 20.2፣ ጭራ 21.5፣ ደምቢ ዶሎ 42.8፣ ዲላ 18.8፣ 19.4፣ ኢጃጂ 26.2፣ 21.5፣ ፉኙዶ 26፣ ጋምቤላ 21.2፣ ጋቲራ 18.6፣ 33.4፣ 33.4፣ 44.6፣ ወሊሶ 25.1፣ ጊዳ አያና 32.1፣ 21.6፣ ጊምቢ 36.6፣ 26.7፣ 32.5፣ 28.1፣ ጅግጅጋ 20.5፣ 20.8፣ ላይብር 20.1፣ ሊሙ ገነት 22.5፣ ማሻ 34.5፣ 26.6፣ ነጆ 24.2፣ 23.5፣ 34.5፣ እንዲሁም ሻምቡ 47.3 ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።


በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ13 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክርምት ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 42.8-69 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ነቀምት፣ አንገር ጉቲን፣ አየሁ፣ ሻምቡ፣ ቦሬ፣ ጋቲራ፣ ደምቢ ዶሎ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ምስል፡1 ከጁን 1-10 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ35 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፣ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ከአማራ ከአማራ ክልል ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ምዕራብ ኦሞ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጌዲዮ፣ የደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ፣ ኮሬ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ኮንሶ፣ አሪ፣ ጋርዱላ ዞኖች ከሱማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ፋፈን እና የሲቲ፣ ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬ ደዋና ሐረር ላይ ከ11-10 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ምስራቅ ሓረርጌ፣ ከአማራ ከአማራ ክልል ምስራቅና ምዕራብ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ምዕራብ ኦሞ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጌዲዮ፣ ከሱማሌ ክልል ፋፈን እና የሲቲ፣ ዞኖች፤ ድሬ ደዋና ሐረር ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

በሌላ በኩል በአቦቦ፣ በአሶሳ፣ በአዋሽ አርባ፣ በአይሻ፣ በባቲ፣ በብላቴ፣ በቻግኒ፣ በጨፋ፣ በጨዋቃ፣ በድሬ ዳዋ፣ በፉኙዶ፣ በጋምቤላ፣ በገዋኔ፣ በጎዴ፣ ጎንደር፣ በቀብሪዳህር፣ ላይብር፣ በመኢሶ፣ በመተሃራ፣ በመተማ፣ በምዕራብ አባያ፣ በሰመራ፣ በሻምቡ፣ በሸርቆሌ፣ ሸዋሮቢት እና በቴፒ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 33.4 እስከ 44.3 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል፡፡


Ethiopian Meteorology In



ስልክ+2511155383949ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 1.2 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት ነበራቸው፡፡ በመሆኑም የነበረው የእርጥበት ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል አንፃር አስቀድመው የተዘሩና በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግም ሆነ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች፣ የመኸር ወቅት የመካከለኛ ጊዜ ሰብሎችን የማሳ ዝግጅት ለማከናወን እንዲሁም ለተለያዩ የቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአርብቶ አደርና በከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው አነስተኛ እርጥበት ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ነበረው (ካርታ 4) ፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 1.3 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የጁን የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው የስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው ዋቤ ሸበሌና ኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን አግኝተዋል። ይህም የእርጥበት ሁኔታ በየተፋሰሶቹ በሚገኙ ግድቦች፣ ሰው ሰራሽ የውሃ መያዥያዎች እንዲሁም የከርሰ ምድር እና የገጸ ምድር የውሃ አቅምን ከማጎልበት አንጻር ጥሩ አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ (ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፤ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በጁን ወር ውስጥ የተቀሩትን የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ያዳርሳል፡፡ በጁን በመደበኛው ሁኔታ የሚታየው የዝናብ መጠንና ስርጭት የተሻለ መልክ የሚኖረው ከወሩ ከመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ጀምሮ ነው። በወሩ በመደበኛው ሁኔታ የሚጠበቀው አማካይ የዝናብ መጠን በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና ሰሜን ምዕራብ ስፍራዎች ላይ ከ100-300 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ15-24 ቀናት ያህል ይዘንባል። ይሁንና በመካከለኛው፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን ከ30-100ሚ.ሜ የሚደረስ ዝናብ ከ3-16 ቀናት ያህል ይዘንባል። ከክረምት ወቅት ዝናብ ድርሻ አኳያ በጁን የደቡብ ምዕራብና የምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች እስከ 30% የሚሆነውን የወቅቱን የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ። በመደበኛ ሁኔታ በጁን ሁለተኛዉ አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብና በመካከለኛው የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮልጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡

### 2.1 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በጁን የሁለተኛዉ አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር አስዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀን ወደ ቀን እየተስፋፉና እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም፤ በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 1)። ስለሆነም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብና በመካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆንና፤ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ደግሞ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁን 11-20, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

### 2.2 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ

በሚቀጥሉት ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ ከባድ (ከ1-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት ቀናቶች ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና የሚያገኙት የዝናብ መጠን

| ክልል | ዞን | የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| አሮሚያ | ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| | ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | ምዕራብ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ ዞኖች የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | የሰሜን እና መካከለኛዉ ጎንደር፣ ዋግ ህምራ፣ ሰሜን እና የደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |




ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

| | | |
|---|---|---|
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ባስኬቶ፣ ጌድዮ እና ኮሬ፣ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ፋፈን፣ ኤረር፣ ነጎብ፣ ጃራር፣ አፍዴር፣ ዳዋ፣ ሊበን፣ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## 2.3 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በጁን የሁለተኛዉ አስር ቀናት ከሚኖረው ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ በተለይም የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በአፋር ክልል፣ በሰሜን ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ሊይ ከ32 እስከ 41 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን አሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ (ካርታ 7)፡፡





ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጁን 11-20, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2.4 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የጁን ሶስተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በይበልጥ እየተጠናከሩ የሚሄዱበትና ከዚህም ጋር ተያይዞ ሁሉንም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ ቦታዎችን የሚያዳርሱበት ጊዜ ነው፡፡




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከጁን 21-30, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

በመጪዎቹ የጁን ሶስተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 8)። ከዚሁ ጋር በተያያዘም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በመካከለኛዉና በምስራቅ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄድ ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8)፡፡

## 2.5 እ.አ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በተለይም በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ ይኖራቸዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ ለወቅቱ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ በአመዛኙ አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ቢሆንም ሊኖሩ የሚችሉ ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የመኸር አምራች ዞኖች** | | | | |
| ቄለም ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ የምስራቅ እና የምዕራብ ጎጃም፣ ምዕራብ እና ደቡብ ጎንደር፣ አዊ ፣የባህርዳር ዙሪያ፣ አኘዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ ፣ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የአፈር ወስጥ እርጥበት መሻሻል<br>• ለረጅም ጊዜ ሰብሎች እድገትና የአጭር ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት<br>• የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት መሻሻል<br>• ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት | • የአፈር እርጥበት መብዛት፣ የማሳዎች መጨቅየት እና የውኃ መተኛት<br>• ውሃ ገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ሰብሎች ላይ የአፈር መታጠብ | • የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም የማሳ ዝግጅት ማከናወንና ዘር መዝራት<br>• የውሃ ማንጣፈፍያ እና የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ከወዲሁ በማዘጋጀት<br>• የማዳበሪያ አጠቃቀምን በትክክለኛው ሰዓት መተግበር<br>• የእርሻ ድግግሞሽን መቀነስ |
| ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና፣ አርሲ፣ ምስራቅና ምእራብ ሐረርጌ፣ የምዕራብና የሰሜን ምዕራብ ትግራይ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለመኸር እርሻ ስራ እንቅስቃሴ ለማከናወን<br>• ለረጅም ጊዜ ሰብሎች እድገት<br>• የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት መሻሻል<br>• ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት | • ከፍተኛ ትነት በሚኖርባቸዉ አካባቢዎች መጠነኛ የሆነ የአፈር ዉስጥ እርጥበት መኖር | • የእርጥበት እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የአፈርና የውሃ እቀባ ስራ ማከናወን<br>• የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል |
| **በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውና የመኸር አብቃይ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ዋግ ህምራ፣ ሰሜን እና የደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ፣ የደቡብ ትግራይ ዞኖች ፣ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬደዋ እና ሐረሪ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ኤረር፣ ጃራር፣ ፋፈን ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለበልግ ሰብሎች ፍሬ ማፍራት<br>• ለመኸር ግብርና እንቅስቃሴ የማሳ ዝግጅትና ዘር ለመዝራት<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • የሚኖረው እርጥበት ለሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን<br>• ደረቅ ሰሞናት መኖር<br>• ከፍተኛ ትነት መኖር | • የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም የመኸር የማሳ ዝግጅትና የዘር መዝራት ማከናወን<br>• የአፈርና የውሃ እቀባ ማከናወን<br>• የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል |



ስልክ+2511155383944ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

| በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ፣ ሁሉም የሲዳማ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ሰብል አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች ለተዘሩ የበልግ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራት<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት<br>• የዝናብ ውኃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም | • ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውሃ በማሳዎች ላይ መተኛት<br>• የአፈር መሸርሸር | • ረባዳማ በሆኑ ማሳዎች ላይ የእርጥበት መብዛት እና ውሃ በሰብሎች ላይ መተኛትን ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ይህንን ለመከላከል የሚያስችሉ የውሃ ማንጣፈፍ ስራዎችን መስራትና የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን በማዘጋጀት የቅድመ ጥንቃቄ ስራ መስራት<br>• የአፈርና የውሃ እቀባና የእርከን ስራ ማከናወን |
| ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ነጎብ፣ አሪ ፣ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለተዘሩ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራት<br>• የዝናብ ውኃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት | • ከፍተኛ ትነት መኖር<br>• ደረቅ ሰሞናት መኖር<br>• የሚኖረው እርጥበት ለሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን | • የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል |

## 2.6 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውኃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣይ አስር ቀናት የክረምት ወቅት መጀመሩን ተከትሎ በአብዛኛው እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። በሚቀጥሉት ቀናት የሚኖረው አዎንታዊ የእርጥበት ሁኔታ በአግባቡ ለመጠቀምና አሉታዊ ሁኔታን ለመቀነስ ከታች የተሰጠውን የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ በአግባቡ መተግበር ያስፈልጋል፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውኃ ተፋሰሶች | የሚጠበቀው የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| አብዛኛው የላይኛው እና የመካከለኛው<br>• ኦሞ ጊቤ<br>• ስምጥ ሸለቆ<br>• ባሮ አኮቦ<br>• አዋሽ<br>• ተከዜ<br>• አባይ<br>አብዛኛው የላይኛው<br>• ገናሌ ደዋ<br>• ዋቤሸበሌ | ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት | የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መሻሻል<br>• የከርሰ ምድር የውኃ መጠን መሻሻል<br>• የመስኖም ሆነ የሃይል ማመንጫ ግድቦች ውኃ መጠን መሻሻል<br>• በሁሉም አካባቢ የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን መሻሻል | ስጋት መጨመር<br>• የውሃ ብክለት ስጋት<br>• | • የጎርፍ የፍሳሽ መውረጃዎች ቦዮችን ማፅዳት<br>• የጎርፈ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት ዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• የጎርፍ ተጽዕኖ ትንበያዎችንና ምክረ ሀሳቦችን በየጊዜው መከታተል |
| የመካከለኛው እና የታችኛው<br>• አዋሽ<br>• ገናሌ ደዋ<br>• ዋቤሸበሌ<br>• ኦጋዴን | መጠነኛ እርጥበት | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት በመጠኑ መሻሻል<br>• የጎርፍም ሆነ የደለል ስጋት መቀነስ | • ከፍተኛ ትነት<br>• ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት<br>• ዝቅተኛ የውኃ ፍሰት<br>• እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች የውሃ እጥረት | • የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል መጠቀም<br>• ወራጅ የዝናብ ውኃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• ከቤት ጣራ ላይ ውኃ የማሰባባሰብ ማጠራቀም |
| በአብዛኛው ታችኛው<br>• ኦጋዴን፣ አይሻ<br>• መረብ ጋሽ<br>• አዋሽ<br>• ገናሌ ደዋ<br>• ዋቤሸበሌ<br>• ኦጋዴን | ደረቅ ሁኔታ | • የጎርፍም ሆነ የደለል ስጋት አለመኖር | • የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ የውኃ ማጠራቀሚያዎች የውኃ መጠን መቀነስ | • የውኃ እጥረት በሚገጥማቸው አካባቢዎች የውኃ ተደራሽነትን ማረጋገጥ<br>• የሚገኘውን ውኃ በቁጠባና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ማስተዳደር |



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et